

# ምዕራፍ 14

# ለወላጆች እና ለአሳዳጊዎች ድጋፍ

በሁሉም ዓለም የሚገኙ ወላጆችና የቤተሰብ አባላት ታዳጊ ልጆቻቸውን ተንከባክበው ለማሳደግ በጣም ጠንክረው ይሰራሉ፡፡ በዚህ ላይ መስማት የማይችል ልጅ ያለው ቤተሰብ ደግሞ ልጁ ከሌሎቹ እኩል ለማደግ የሚያስችለውን ነገሮች ሁሉ ማግኘት እንዲችል ተጨማሪ ጥረት የማድረግ ሃላፊነት አለበት፡፡ በሕፃኑ ህይወት ላይ ትልቅ ለውጥን ማስገኘት የሚቻለው ይህ በተጨማሪነት የሚከናወነው ሥራ ነው፡፡ ነገር ግን ለወላጆች በጣም አድካሚና አስጨናቂ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ምዕራፍ ወላጆችና አሳዳጊዎች የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች መቋቋም እንዲችሉና ራሳቸውንም ሆነ መስማት የተሳናቸው ልጆቻቸውን መንከባከብ እንዲችሉ ለመርዳት ጠቃሚ መረጃዎችን ይዟል፡፡




ሕይወታችን ከልጆቻችን ጋር የተቆራኘ በመሆኑ፣ በእነሱ ላይ የሚደርስ ማንኛውም ነገር ሁሉ በእኛም ላይ ተፅዕኖ ያደርጋል፡፡ የብዙዎቹ መስማት የተሳናቸው ሕፃናት ወላጆች ወደፊት ስላለው የልጆቻቸው ሁኔታ ተስፋ ይቆርጣሉ፡፡ ነገር ግን ወላጆች በመተባበር አንዱ ሌላውን ማገዝ ቢችሉ፣ የመስማት የተሳናቸውን ልጆቻቸውን ህይወት ማሻሻል ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም አንድ ላይ ሆነው ማህበረሰባቸውም ከጎናቸው እንዲቆም ለማድረግ ከሰሩ፣ የመስማት ችግር ላለባቸው ህፃናት ሁሉ የተሻለ ድጋፍ ማድረግ ይችላሉ፡፡

## ልጅዎ በደንብ መስማት እንደማይችል ለመጀመሪያ ጊዜ ሲያውቁ

ወላጆች የልጃቸውን መስማት አለመቻል ለመጀመሪያ ጊዜ ሲያውቁ ይበሳጫሉ:: ሁኔታው ሌሎች የቤተሰብ አባላትንና ዘመዶችንም ጭምር የሚያሳዝናቸው ሊሆን ይችላል:: ይህ ያለ ነገር ነው:: ለመጀመሪያ ጊዜ የሚከተሉት ስሜቶች ሊጋጥሙ ይችላሉ:–

- ምን ላድርግ ብሎ መጨነቅ




- ክህደት





- ብቸኝነት





- ልጅዎ መስማት የተሳነው በመሆኑ ሀፍረት





- እንደ እጣ ፋንታ ወይም ቅጣት አድርጎ መቀበል




- ፍርሃት – መስማት የተሳነው ማለት ምን ማለት እንደሆነና ስለወደፊቱ ጊዜ መፍራት





- ቁጣ – ስለሆነው ነገር




- ፀፀት– ምን በደል ፈፅሜ ይሆን




- ሀዘን፣ ተስፋ መቁረጥ፣ ወይም ስሜት አልባ መሆን (ጭንቀት)



## የራስዎን ስሜት መረዳት

ወላጆች፣ ሌሎች የቤተሰብ አባላት፣ እና ሞግዚቶች የተወለደው ሕፃን መስማት የተሳነው በመሆኑ የተለያዩ ስሜቶች ይሰማቸዋል፡፡ ነገር ግን አንዱ በሌላው ላይ ሳይፈርድ ማንኛውም ሰው የሚሰማውን ስሜት በራሱ እንዲወጣው ዝም ማለቱ ይሻላል፡፡




አንዳንድ ስሜቶች ለምሳሌ ጭንቀት፣ ብቸኝነት፣ ወይም ፍርሃት ከጊዜ በኋላ ቀስ በቀስ እየቀነሱ ይሄዳሉ፡፡ ጊዜ እያለፈ ሲሄድ መስማት የተሳናት ሕፃንም ልክ እንደሌሎች ህፃናት ሁሉ ለፍቅር፣ ለመውደድ፣ ለሥነ ሥርአትና ለመማር ተመሳሳይ ፍላጐቶች እንዳሏት ማወቅ ይችላሉ፡፡




እነዚህ ስሜቶች ለልጅዎ ወሳኝ በሆኑ ጊዜያት፣ ለምሳሌ ት/ቤት ስትገባ፣ ተመልሰው ይመጣሉ፡፡ ይህ ምንም ችግር የለውም፡፡ ይህ ማለት የልጅዎን መስማት አለመቻል ለመቀበል ሌላ ወቅት እያሳለፉ ነው ማለት ነው፡፡


እነዚህ ከባድ የሆኑ ስሜቶች በልጅዎ ህይወት ላይ የተሻለ እርምጃ እንዲወስዱ ይረዳዎታል፡፡ ለምሳሌ ብቸኝነት ሲሰማዎ፣ በማህበረሰብዎ ውስጥ የሚገኙትን መስማት የተሳናቸውን ሰዎች ወይም ሌሎች መስማት የተሳናቸው ሕፃናት ያሏቸውን ወላጆች እንዲያገኙ ይገፋፋዎታል፡፡ ንዴት ሲሰማዎ ደግሞ ሌሎች ወላጆችን አስተባብረው፣ መንግስት መስማት ለተሳናቸው ሕፃናት የትምህርት አገልግሎት እንዲሰጥ ለመጠየቅ ኃይል ሊሆንዎት ይችላል፡፡

ልጅዎ በደንብ መስማት አለመቻሏን ሲቀበሉት፣ ባለችበት ሁኔታ መውደድ ይጀምራሉ፡፡ እሷም ልክ እንደ ሌሎች ልጆች በተመሳሳይ ሁኔታ ብዙ ድጋፍና ደስታን ትሰጥዎታለች፡፡



## የአሳዳጊዎችን ጭንቀት መቋቋምና ማቃለል

የአንድ ሕፃን ወላጅ መሆን ማለት ከባድ ስራ ነው፡፡ የእርሰዎ ልጅ ደግሞ በደንብ መስማት የማይችል ወይም መስማት የተሳነው ከሆነ የበለጠ ብዙ ስራ ይጠብቅዎታል ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ የሚሰሙ ሕፃናት ሰዎች ሲያወሩ ብቻ በመስማት መማር ሲችሉ፣ መስማት ለተሳነው ሕፃን ግን ቤተሰቦቹ ሊያስተምሩት ያስፈልጋል፡፡




ለዚህ ዓይነቱ ተጨማሪ ስራ ጊዜንና ኃይልን ማግኘቱ ሊከብድ ይችላል፡፡ አንዳንድ ወላጆች የዚህ ዓይነቱን ጭንቀት እንዴት መቋቋም እንደቻሉ ከዚህ ቀጥሎ በምክር መልክ ቀርቧል፡፡

## ተንከባካቢዎችን መንከባከብ



ወላጆችና ሞግዚቶች ሕፃናትን በደንብ መንከባከብ የሚችሉት ራሳቸውም ዘና ማለት ሲችሉ ነው፡፡ ቀላል የሆኑ ድርጊቶች ለምሳሌ ወደ ገበያ መሄድ፣ ዘመዶችን ወይም ጓደኞችን መጐብኘት፣ ከጓደኞች ጋር ማውራት፣ ሰውነትን መታሸት፣ ወይም በማህበራዊ ቡድኖች ውስጥ መሳተፍ ሊረዱ የሚችሉ ናቸው፡፡ ማስታወስ የሚያስፈልግዎ ነገር ቢኖር ልጆችዎን መርዳት የሚችሉት የራስዎ አካላዊና አእምሮአዊ ጤንነት ሲጠበቅ ነው፡፡




አንዳንድ ጊዜ ወላጆች ተሰባስበው ስለ ችግሮቻቸው ሲያወሩ መንፈሳቸው ሊታደስ ይችላል፡፡ አንዳንዶቹ ሰዎች ግን ምናልባት በቡድን ሆነው ሲያወሩ ስለ ራሳቸው መናገር አይፈልጉ ይሆናል፤ እንደዚህ ዓይነቶቹ ሰዎች የራሳቸውን ሁኔታ ሊገልፁላቸው የሚችሉ መዝሙሮችን ሊዘምሩ፣ ግጥሞችን ሊደርሱ፣ ወይም ታሪኮችን ሊፅፉ ይችላሉ፡፡ አንዳንድ ሰዎች ደግሞ ሃሳቦቻቸውንና ስሜቶቻቸውን ቃላትን ሳይጠቀሙ ስዕሎችን በመሳል መግለፅ ይችላሉ፡፡ ይህንን ለማድረግ የግድ የስዕል ሙያ ያላቸው ሊሆኑ አያስፈልግም፡፡

አንዱ ሌላውን መንከባከብ እንደሚያስፈልግ ያስታውሱ፡፡ ወላጅ መሆን ከባድ ስራ ነውና፡፡





ብዙ ማህበረሰቦች ሰውነታቸውንና አእምሮአቸውን ለማረጋጋትና ውስጣዊ ኃይልም ለማግኘት ሊረዷቸው የሚችሉ እምነቶችና ባህሎች አሏቸው:: እነዚህን ባህሎች በመተግበር ለራስዎ የተሻለ ጥንቃቄ ማድረግ ይችላሉ::



ፀሎት



በሃሳብ መመሰጥ



ጁዶ/ካራቴ (አካላዊ እንቅስቃሴዎች)

# የወላጆች ማህበራት

## የወላጆች ማህበር የሂሩትን ህይወት ቀየረ

ሮዛ የምትባል አንዲት እናት፣ ልጇ ሂሩት የሆነ ችግር እንዳለባት መጠርጠር ጀመረች::ሂሩት ስሟ ሲጠራ መልስ አትሰጥም፣ ትንሽ ደንገጥ የምትለውም ለከባድ ድምጾች ብቻ ነበር::

ስለ ልጇ የተጨነቀችው ሮዛ፣ ሂሩትን በ16 ወራት ዕድሜዋ ወደ ሐኪም ወሰደቻት:: ሐኪሙምም በቀዘቀዘ መንፈስ “ልጅሽ ምንም አትሰማም፣ ዕድሜዋ 5 ዓመት ሲሞላ መልሰሽ አምጫትና በዚያን ጊዜ ምን እንደምናደርግ እናያለን” አላት:: ሮዛ ከበፊቱ የበለጠ በጣም በፍርሃት ተዋጠች::




ወደ ቤቷ ስትመለስ በመንገድ ላይ ያገኘቻት አንድ ጓደኛዋ፣ በከተማቸው ያለውን የወላጆች ማህበርን ብታማክር ሊረዷት እንደሚችሉና ሄዳ ቀጠሮም ብትይዝ የሚሻል መሆኑን ነገረቻት:: የወላጆች ማህበሩም የአካል ጉዳት ያለባቸው ልጆቻቸው የተሟላ ዕድገት እንዲኖራቸው በሚፈልጉ ወላጆች የተመሰረተ ማህበር ነው::


በወላጆች ማህበሩ ውስጥ ያለው ሐኪምና ሰራተኞችም ልጇ መስማት የተሳናት እንደሆነች ከበፊቱ ጋር ተመሳሳይ ውጤት ለሮዛ ቢሰጧትም፣ ግን ስለ ወደፊቱም ሁኔታ ተስፋ ሊሰጧት ችለዋል:: ሂሩትን ልዩ እርዳታና ተጨማሪ ድጋፍ ከቤተሰቦቿ የምታገኝ ከሆነ ልክ እንደማንኛውም በትክክል መስማት እንደምትችል ሕፃን ማደግ የምትችል መሆኗን ገለፁላት:: በዚያ ማህበር ውስጥ ከሚገኙት ከሌሎች ወላጆች ድጋፍ በማግኘቷ፣ ሮዛ በሂሩት ህይወት ላይ ለውጥ ማምጣት እንደምትችል ተማመነች::

አሁን ሮዛ የወላጆች ማህበሩ ንቁ አባል ስትሆን እሷ በሚያስፈልጋት ጊዜ ታገኝ የነበረውን እርዳታና አጋርነት ለሌሎች ወላጆች መስጠት ጀምራለች::

ድጋፍና እንክብካቤ ላደረጉላት ለቤተሰቦቿና ለወላጆች ማህበሩ አባላት ምስጋና ይግባቸውና ሂሩት ራሷን መግለፅ የምትችል፣ ራሷን የምትንከባከብ፣ ደስተኛ፣ ብልህ፣ እና በራሷ የምትተማመን ልጃገረድ ለመሆን በቅታለች:: ለመግባባትና መደበኛ ት/ቤት ገብታ ለመማር ችላለች::



## ማህበርን መጀመር




በማህበረሰብዎ ውስጥ መስማት የተሳናቸው ልጆች ያሏቸው ሌሎች ወላጆች እንደሚኖሩ የሚያውቁ ከሆነና ነገር ግን የወላጆች ማህበር በዚያ አካባቢ ከሌለ እርስዎ እንዲጀመር ማድረግ ይችላሉ፡፡ አንዳንድ በጣም ጠንካራና ንቁ ተሳትፎ ያላቸው የወላጆች ማህበራት የተጀመሩት በግለሰቦች ሃሳብ አመንጪነት ነው፡፡ ወላጆች በቡድን ሲሆኑ ለችግሮቻቸው መፍትሄ ለማግኘት ተግተው መስራት ይችላሉ፡፡ ወላጆች በአንድነት ሆነው ከሰሩ፣ በተናጠል ከሚሰሩት የበለጠ ወደ ውጤት የሚመራቸውን ሥራን አቀላጥፈው መስራት ይችላሉ፡፡

- ማህበሩን መመስረት የሚፈልጉ 2 ወይም ከዚያ በላይ የሚሆኑ ወላጆችን ወይም ሞግዚቶችን ይፈልጉ፡፡ መስማት የተሳናቸው ልጆች ያሏቸውን ወላጆች ማግኘት ካልቻሉ፣ ሌላ የአካል ጉዳተኛ የሆኑ ልጆች ያሏቸውን ወላጆች ሊያገኙ ይችላሉ፡፡ ወይም በአቅራቢያዎ ባሉ ማህበረሰቦች ውስጥ የመስማት የተሳናቸው ልጆች ወላጆች መኖር አለመኖራቸውን ከአንድ የጤና ባለሙያ መጠየቅ ይችላሉ፡፡

- የት እና መቼ መሰብሰብ እንደምትችሉ ያቅዱ፡፡ ሰዎች በነፃነት ለማውራት የሚመቻቸውን ቦታ ቢመርጡ ጥሩ ነው፡፡ ለምሳሌ፣ በት/ቤት በአንድ ክፍል ውስጥ፣ በጤና ጣቢያ፣ በቀበሌ ጽ/ቤት፣ በሀይማኖታዊ መሰብሰቢያ ቦታዎች መሆን ይችላል፡፡ በመጀመሪያው ስብሰባችሁ ቀን፣ ለምን መሰብሰብ እንደፈለጋችሁና ለወደፊቱ ምን ለመስራት ተስፋ እንደምታደርጉ ተወያዩ፡፡

- የመጀመሪያዎቹን ጥቂት ስብሰባዎች አንድ ሰው ሊመራው ይችላል፡፡ ነገር ግን አንድ ሰው ስለ ቡድኑ ውሳኔን መወሰን የለበትም፡፡ ሁሉም ሰው ለመናገር እድል ሊኖረው ያስፈልጋል፡፡ ውይይቱ ለስብሰባው በተያዙት አጀንዳዎች ዙሪያ ብቻ እንዲሆን የተቻለዎትን ሁሉ ይሞክሩ፡፡ ከመጀመሪያዎቹ ጥቂት ስብሰባዎች በኋላ ቡድኑን ተራ በተራ ለመምራት ሞክሩ፡፡ እያንዳንዱን ስብሰባ የተለያየ ሰው የሚመራው ከሆነ ለመናገር የሚያፍሩ አባላትም ተሳትፎ እንዲያደርጉ ሁኔታዎቹ ሊያስገድዱአቸው ይችላሉ፡፡

## እርስ በርስ መረዳዳት

ሰዎች እርስ በርሳቸው በደንብ ቢተዋወቁም እንኳ ስለ ስሜቶቻቸው፣ ስለ ልምምዶቻቸው፣ እና መስማት የተሳነውን ሕፃን በማሳደግ ዙሪያ ስላሉት ችግሮች በነፃነት ለመነጋገር ጊዜ ሊወስድባቸው ይችላል፡፡ እነዚህን ጉዳዮች ለመወያየት ከሰዎች ጋር በደንብ መለማመድንና መተዋወቅን ይጠይቃል፡፡



የቡድኑ አባላት እርስ በርሳቸው በነፃነት ማውራትና መተማመንም እንዲችሉ የሚረዱ ሃሳቦች ከዚህ በታች ቀርበዋል፡–

***በሰዎች ላይ ሳይፈርዱ ዝም ብለው በፅሞና ያዳምጧቸው፡፡*** እርስዎ ሲናገሩ ሌሎች ሰዎች እንዲያደምጥዎ እንደሚፈልጉ ሁሉ ሌሎች ሰዎች ሲያወሩ እርስዎም በተመሳሳይ ሁኔታ ያዳምጧቸው፡፡




***ምን ማድረግ እንደሚያስፈልጋቸው ለሰዎች መንገር አይሞክሩ፡፡*** ሰዎች የሚሰማቸውን ስሜት ከተረዱላቸው እና የራስዎንም ልምድ ካካፈሏቸው፣ እንደረዱአቸው ይቆጥሩታል፡፡ ነገር ግን እያንዳንዱ ሰው ስለ ራሱ ልጆች እንክብካቤ ራሱ ውሳኔ ሊሰጥ ያስፈልጋል፡፡




*የእያንዳንዱ ሰው የግል ህይወት የሆኑትን ጉዳዮች ያክብሩ::* በማህበሩ ውስጥ የተነገረውን ጉዳይ አውጥተው ለሌሎች ሰዎች አያውሩ (ከእያንዳንዱ ሰው ሙሉ ፈቃደኝነት እስካላገኙ ድረስ)::




## ለመተግበር ማቀድ

ተባብረው የሚሰሩ ወላጆች ችግሮችን ለመፍታት ተግባራዊ እርምጃዎችን መውሰድ ይችላሉ:: እርምጃዎችን በየደረጃው ለመውሰድ የሚረዱ ሃሳቦች ቀጥሎ ቀርበዋል፡—

1. ከሁሉም በላይ ቅድሚያ ሊሰጠው ያስፈልጋል ብሎ ቡድኑ የሚያምንበትን ዋነኛ ችግር ምረጡ:: በፍጥነት ተሰርተው መስተካከል የሚያስፈልጋቸው ብዙ ነገሮች ቢኖሩም፣ ማህበሩ በስራው የበለጠ ውጤታማ መሆን የሚችለው እያንዳንዱን ችግር በየተራ ለመፍታት ሲሰራ ነው:: በመጀመሪያ፣ ማህበሩ ራሱ በፍጥነት ሊፈታው የሚችለውን ችግር ይውሰዱ:: ከዚያ በኋላ፣ ማህበሩ በደንብ ተባብሮ መስራት ሲችል፣ በጣም በተወሳሰቡ ችግሮችም ላይ መስራት ይቻላል::



2. ችግሩን እንዴት መፍታት እንደምትችሉ ወስኑ:: ችግሩን ለመፍታት የሚያስችሉ ዘዴዎችን በብዛት ከዘረዘራችሁ በኋላ፣ ከማህበራችሁ አቅምና ሀብት ጋር በደንብ ሊሄድ የሚችለውን አንዱን መፍትሄ ምረጡ::




3. ዕቅድ አዘጋጁ:: *ሥራውን ለመጨረስ የማህበሩ አባላት የተለያዩ ነገሮችን ማድረግ ይኖርባቸዋል::* እያንዳንዱ ተግባር መቼ ተሰርቶ ማለቅ እንዳለበት ቀኑን ለመወሰን ሞክሩ::




4. በምትገናኙበት ጊዜ፣ *ሥራው እንዴት እየተካሄደ እንደሆነ ተነጋገሩ::* ችግሮች ከተፈጠሩ፣ እንደ ሁኔታው እየተወያያችሁ ዕቅዳችሁን አሻሽሉ::



## ጥቂት ድጋፍ ሰጪ ሀብት ያለው ማህበር ለውጥ ማስገኘት ይችላል

እኛ የምናምነው ማህበረሰቡ በሙሉ ማለትም ጐረቤቶች፣ መንደሩ፣ ከተማው፣ ወይም አገሩ በሙሉ የአካል ጉዳተኛ ሕፃናት ቤተሰቦችን የመርዳት ሃላፊነት አለበት ብለን ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ግን ሰፊው ማህበረሰብ ይህንን ሃላፊነት እንዲቀበል ለማድረግ የወላጆችን ተባብሮ መስራትና ብርቱ ጥረትን ይጠይቃል፡፡ ሰዎች ከተባበሩና ሀብታቸውን በአንድ ላይ ካቀናጁ እንቅፋቶችን ሁሉ በማለፍ ምንም ባልነበረበት ቦታ የሆነ ነገር ማድረግ እንደሚቻል በደቡብ አፍሪካ የሚገኙ ወላጆች በተግባር ማሳየት መቻላቸውን የሚቀጥለው ታሪክ ይነግረናል፡፡

### ሀብትን መገንባት – የቆራጥነት ኃይል

በደቡብ አፍሪካ በሚገኝ አንድ ከተማ፣ የአካል ጉዳት ያለባቸው ህፃናት ከሌሎች ሕፃናት ጋር አብረው መጫወትና አብረው መማር ያልተለመደ ነገር ነበር፡፡ ብዙዎቹ ወላጆች ከቤታቸው ወጥተው ሥራ መስራት አልቻሉም ነበር፤ ምክንያቱም በአቅራቢያቸው ያሉት የመዋዕለ ሕፃናት ማዕከሎች የእነሱን ልጆች ለመቀበል ፈቃደኛ አልነበሩም፡፡ ጥያቄውን ለሚያቀርቡት ወላጆች ማዕከሎቹ የሚመልሱላቸው መልሶች “ምን ማድረግ እንደሚገባን እናንተ አትነግሩንም!” እና “እነዚህን ሕፃናት ለማስተማር የተመቻቸ ሁኔታ ምንም የለንም” በማለት ነበር፡፡

የወር ደመወዝ የሚያስገኝ ስራ የሌላቸውና አብዛኞቹ የመደበኛ ትምህርት የሌላቸው እናቶች በአንድነት ተሰባስበው፣ የአካል ጉዳተኛ ለሆኑት ልጆቻቸውና ለቤተሰቦቻቸውም ጭምር አንድ ጠቃሚ ነገር ለመስራት ማህበር አቋቋሙ፡፡ ከእነሱ ውስጥ አንድ ወይም ሁለት የሚሆኑት ሁሉንም ሕፃናት እንዲጠብቁና ሌሎቹ ሥራ እንዲፈልጉ ወሰኑ፡፡

እናቶቹ ልጆቻቸውን ለመንከባከብ መርሀ ግብር አዘጋጁ፡፡ ከእነሱ ውስጥ አንዷ ምግብ ለማዘጋጀት ፈቃደኛ ሆነች፡፡ አንዷ አስተማሪ ሆነች፡፡ ሌሎቹ በውጪ ሥራ ማፈላለግ ጀመሩ፡፡ ሥራ ፈልገው ያገኙት ወላጆች ልጆቻቸውን ለሚጠብቁና እያደገ ላለው የመዋዕለ ሕፃናቱ ማዕከል ገንዘብ ማዋጣት ጀመሩ፡፡ ሥራ ያላት አንዷ ወላጅ ለልጆቹ መፅሐፍት ገዛች፡፡




አንድ የማህበራዊ ሠራተኛ እነዚህ ወላጆች የሚያደርጉትን ሰምታ ለማየት መጣች፡፡ ከዚያም የአካባቢው መንግስት በማዕከሉ ውስጥ ለሚሰሩት እናቶች ትንሽ ገንዘብ እንዲሰጣቸው ማድረግ ቻለች፡፡

እናቶቹ በነበራቸው ጥረት፣ ሀብት፣ ቁርጠኝነት – ለልጆቻቸው የመዋዕለ ሕፃናት ማዕከል ሊገነቡና ለራሳቸውም ገቢ ሊያገኙ ችለዋል!

## ለውጥ ለማምጣት ተባብሮ መስራት

የወላጆች ማህበራት በብዙ ፕሮጀክቶች ላይ ይሰራሉ፡፡ የቤተሰቦች የኤኮኖሚ ሁኔታዎች፣ የማህበረሰቦች አመለካከቶች፣ ወይም የመንግስት ህጐችና አገልግሎቶች መስማት ለተሳናቸው ሕፃናት ምቹ ሆነው እንዲሻሻሉ ወላጆች መስራት ይችላሉ፡፡ ለልጆቻቸው በቂ ድጋፍ ሊሰጡ የሚችሉ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት የወላጆች ማህበር ሊያደርጋቸው ከሚችላቸው ነገሮች ውስጥ ጥቂቶቹ፡–

- መስማት የተሳናቸውን ሕፃናት ለመርዳት የሚችሉ ፕሮጀክቶችን ማዘጋጀትና ለዚህም የሚውል የገንዘብ ድጋፍ ማፈላለግ፡፡
- ወላጆች አዳዲስ የሥራ ክህሎቶችን እንዲያዳብሩ መርዳት
- ስለ መስሚያ መርጃ መሳሪያ መረጃዎችን ማሰባሰብና መስጠት
- የምልክት ቋንቋን ለማስተማር ሁኔታዎችን ማመቻቸት
- መስማት የተሳናቸውና የሚሰሙ ሰዎች እንዲቀራረቡ ማድረግ



እነዚህ እናቶች የልብስ ስፌት ስለተማሩ የበለጠ ገንዘብ ያገኛሉ፣ በቤታቸው አቅራቢያ መስራት ይችላሉ፣ እንዲሁም ከልጆቻቸው ጋር የበለጠ ጊዜን ማሳለፍ ይችላሉ

ብዙዎቹ የወላጆች ማህበራት ሌላውን የማህበረሰብ ክፍል ስለ መስማት መሳን ለማስተማር ይሰራሉ፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ሥራውን የሚሰሩት መስማት ከተሳናቸው ሰዎች ጋር በመተባበር ነው፡፡ ሰዎች በቀላሉ ስለ መስማት መሳን መረዳት እንዲችሉ ማህበሮቹ ለማስተማር ለምሳሌ፣ እድሮችን፣ የቀበሌ ስብሰባዎችን፣ የሐይማኖት ቦታዎችን፣ እንደዚሁም ወርክሾፖችን፣ የራዲዮ ፕሮግራሞችን፣ ጋዜጦችን፣ መፅሔቶችን፣ ማስታወቂያ ሰሌዳዎችን፣ የመንገድ ላይ ቲያትሮችን፣ እና ፖስተሮችን ለማስተማሪያ መድረክነት መጠቀም ይችላሉ፡፡

መስማት የተሳናቸውን ሕፃናት በተመለከተ ፕሮግራሞች፣ ህጐች እና ፖሊሲዎች እንዲሻሻሉ የወላጆች ማህበራት መንግስትን መጠየቅ ይችላሉ፡፡ ስለልጆቻቸው የትምህርትና የጤና ሁኔታን በተመለከተ በትምህርት ሚኒስቴርና በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የሚሰሩ ባለስልጣናትን ማነጋገር ይችላሉ፡፡ ማህበረሰቡ የሚያስፈልጉትን አገልግሎቶች፣ ወይም ስለ መስማት የተሳናቸው ወይም በደንብ መስማት ስለማይችሉ ሕፃናት ጥበቃ የሚያስፈልጉ ህጐች እንዲዘጋጁና አገልግሎቶች እንዲስፋፉ መጠየቅ ይችላሉ፡፡ ደብዳቤዎችን ይፅፋሉ፣ ወይም የሰዎችን ፊርማ ያስባስባሉ፣ ወይም የመንግስት ባለስልጣናት የልጆቻቸውን ሁኔታዎች ካላሻሻሉላቸው ሰላማዊ ሰልፍ ያደርጋሉ፡፡

